



ጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፲ ፡ ዓ. ፡ ም.

"....በውስጥ ፡ ባሉት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እናንተ ፡ አትፈርዱምን ? በውጭ ፡ ባሉት ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድባቸዋል ፡ ክፉውን ፡ ከመካከላችሁ ፡ አውጡት."

ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ጳውሎስ ፡ ( ፩ ቆሮ ÷ ም ፭ ፡ ቁ ፲፪ )

ፓትርያርክ ፡ አባ ፡ ጳውሎስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋህዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ወገኖቻችን ፡ ላይ ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ክህደትና ፡ ወንጀል ፡ በተመለከተ ፡ ከለንደን ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፥ ማኅበረ ፡ ካህናትና ፡ ምእመናን ፡ የወጣ ፡ የአቋም ፡ መግለጫ ።

## የአቋም ፡ መግለጫው ፡ ዓላማ

1. የዚህ ፡ የአቋም ፡ መግለጫ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ፓትርያርክ ፡ አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰጣቸውን ፡ ኃላፊነት ፡ በመጣስ፤ ከክርስትና ፡ እምነትና ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ በሥልጣን ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ የገዢ ፡ የፖለቲካ ፡ ፓርቲ ፡ ጋር ፡ በማበር ፡ የፈጸሙት ፡ በደል፥ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንን ፡ እየከፋፈለና ፡ ሰላማችንን ፡ እያደፈረሰ ፡ ከመሄዱም ፡ በላይ፤ በአገር ፡ ውስጥና ፡ በውጭ ፡ ያሉትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንድነት ፡ እንዳይኖራቸው ፡ አድርጓል ። ይህን ፡ ችግር ፡ ከሥሩ ፡ ቆርጦ ፡ ለማስወገድና፤ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደቀድሞው ፡ እምነቷ፥ ሥርዓቷና ፡ አንድነቷ ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ ዘላቂ ፡ መፍትሄ ፡ ለማግኘት ፡ ነው ።

2. በዓለም ፡ ዙሪያ ፡ ዛሬ ፡ በአባ ፡ ጳውሎስ ፡ ምክንያት ፡ ተከፋፍላ ፡ አንድነቷኗ ፡ ሕልውናዋ ፡ አስጊ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የወደቀውን ፡ ቅድስት ፡ እናት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንን ፡ በኅብረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድነቷኗ ፡ ሰላሟ ፡ እንዲጠናከር ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ ያሉ ፡ አባቶቿ ፡ ሊቃውንቶቿና ፡ ልጆቿ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጉባኤ ፡ በማዘጋጀት ፡ ውይይት ፡ እንዲጀምሩ ፡ የፍቅር ፡ ጥሪያችንን ፡ ለማቅረብ ፡ ነው ።

# መቅድም

የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋሕዶ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ከምትሰጠው፡ መንፈሳዊ፡ አገልግሎት፡ በተጨማሪ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ ነፃነት፡ አንድነት፡ እኩልነትና፡ ሥልጣኔ፡ ግንባር፡ ቀደም፡ በመሆን፡ ታላቅ፡ አስተዋፅዖ፡ አድርጋለች።

በመሆኑም፡ ከኢትዮጵያውያን፡ ሕልውናና፡ ነፃነት፡ ጋር፡ የተሣሠረ፡ የአኩሪ፡ ታሪክ፡ ባለቤት፡ ነች። በዚህም፡ ምክንያት፡ ከውስጥም፡ ሆነ፡ ከውጭ፡ የሚነሡ፡ የአገሪቱ፡ ጠላቶች፡ በተደጋጋሚ፡ የጥፋት፡ እጃቸውን፡ አንሥተውባት፡ እንደነበር፡ የታሪክ፡ መዛግብት፡ ይመሠክራሉ።

በነዚያም፡ ፈታኝ፡ የታሪክ፡ ምዕራፎች፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ መሪዎች፡ ፍትሕ፡ እንዳይጓደል፡ ደሃ፡ እንዳይበደል፡ ሲመክሩና፡ ሲገሥፁ፤ የአገር፡ አንድነትን፡ የሕዝብ፡ ነፃነትን፡ የሚደፍሩትን፡ እያወገዙ፡ እራሳቸውን፡ ለበጎቻቸውና፡ ለዜጎቻቸው፡ መስዋዕት፡ በማድረግ፡ ሐዋርያዊ፡ የአባትነት፡ ግዴታቸውን፡ ተወጥተው፡ ሕያው፡ በሆነ፡ የታሪክ፡ ቀለም፡ ገድላቸው፡ ተፅፎላቸዋል። ለዚህም፡ በፋሽስት፡ ኢጣልያ፡ ወረራ፡ ፡ ሰማዕትነት፡ የተቀበሉትን፡ ብፁዕ፡ አቡነ፡ ጴጥሮስን፡ በምሳሌነት፡ መጥቀሱ፡ በቂ፡ ነው።

ከዚህ፡ አኩሪ፡ ታሪክ፡ በተጻራሪ፡ በአሁኑ፡ ወቅት፡ በቤተ፡ ክርስቲያናችን፤ በፓትርያርክ፡ ወንበር፡ ላይ፡ በተቀመጡት፡ በአባ፡ ጳውሎስ፡ ኢሃይማኖታዊ፡ አስተዳደርና፤ በመንግሥት፡ መንበር፡ ላይ፡ ከተቀመጠው፡ የፖለቲካ፡ ድርጅት፡ ጋር፡ ባላቸው፡ የተሣሠረ፡ ወዳጅነት፤ በኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ቤተ፡ ክርስቲያንና፤ በአገራችን፡ ከመቸውም፡ ጊዜ፡ በላይ፡ የሚያሳዝንና፡ ሕዝብን፡ የሚያስቆጣ፡ በደል፡ በመፈጸም፡ ላይ፡ ነው።

በአሁኑ፡ ወቅት፤

- ንፁሕ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ከሕፃናት፡ እስከ፡ አዛውንት፡ ደማቸው፡ በግፍና፡ በጭካኔ፡ በገዢው፡ መንግሥት፡ ወታደሮች፡ ሲፈስ፤ በግፍ፡ ሲታፈኑና፡ በዱር፡ በበረሃ፡ ሲጣሉ።
- ለሁለት፡ ሺህ፡ ዓመታት፡ በአንዲት፡ እምነትና፡ ሥርዓት፡ በአንድ፡ አስተዳደር፡ ሥር፡ የቆየች፡ ቤተ፡ ክርስቲያናችን፡ ስትከፋፈል። በብዙ፡ ሺህ፡ የሚቆጠሩ፡ የክርስቶስ፡ በጎች፡ ምእመናን፡ ሲሰናከሉና፡ ከቤተ፡ ክርስቲያናቸው፡ ሲርቁ፤
- ከሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ እስከ፡ ዲያቆናት፡ እንዲሁም፡ ምእመናን፡ ድረስ፡ አገራቸውን፡ ለቀው፡ በግድ፡ ሲሰደዱ።
- በዮዲት፡ ጉዲትና፡ በግራኝ፡ መሐማድ፡ ዘመን፡ ከደረሰው፡ ጥፋትና፡ እልቂት፡ የከፋ፡ በደል፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ላይ፡ ሲፈፀም፤ ታሪካዊና፡ መተኪያ፡ የሌላቸው፡ ገዳማትና፡ አድባራት፡ ሲቃጠሉና፡ ሲመዘበሩ፤
- የአገርና፡ የትውልድ፡ መኩሪያ፡ የሆኑ፡ ዓለምን፡ ያስደነቁ፡ ብርቅና፡ ድንቅ፡ ንዋያተ፡ ቅድሳቶች፡ ሲዘረፉና፡ በገበያ፡ ላይ፡ ሲውሉ፤

የለንደን፡ ደብረ፡ ጽዮን፡ ቅድስት፡ ማርያም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ማኅበረ፡ ካህናትና፡ ምእመናን፡ ከእንግዲህ፡ በትዕግስትና፡ በዝምታ፡ የሚያልፉት፡ አይሆንም።

> በተለይም፡ በስደት፡ የምንገኝ፡ የደብረ፡ ጽዮን፡ ቅድስት፡ ማርያም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ካህናትና፡ ምእመናንን፡ ለመበተን፡ አባ፡ ጳውሎስ፡ ባለፈው፡ ነሐሴ፡ ወር፡ በደብዳቤ፡ ቁጥር P/S/640/97 ለአንግሊካን፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ጳጳሳት፤ ሕንጻ፡ ቤተ፡ ክርስቲያኑን፡ እንዳይሸጡልን፤ በስውር፡ የላኩት፡ ደብዳቤ፤ የተጀመረውን፡ የሕንጻ፡ ግዢ፡ ሂደትና፡ የቤተ፡ ክርስቲያንን፡ እድገት፡ ለማደናቀፍ፡ ላደረጉት፡ ጥረት፤ ዓይን፡ ገላጭ፡ ማስረጃ፡ ነው።

ምንም፡ እንኳ፡ የለንደን፡ ደብረ፡ ጽዮን፡ ቅድስት፡ ማርያም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ እስከ፡ ቅርብ፡ ጊዜ፡ ድረስ፡ አባ፡ ጳውሎስን፡ በማክበር፡ "ብፁዕ፡ ወቅዱስ፡" እያለች፡ ስትጠራ፡ የቆየች፡ ቢሆንም፤

ከላይ፡ የተዘረዘሩት፡ እውነታዎች፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የሚያስጠይቁና፡ በታሪክም፡ ተወቃሽ፡ የሚያደርጉ፡ በመሆናቸው፡ "እውነቱን፡ እውነት፡" ብላ፡ በወቅቱ፡ መመስከር፡ ግዴታዋ፡ ሆኗል።

# የአቋም ፡ መግለጫ ።

1. የለንደን ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቅዱስ ፡ ሲኖዶስ ፡ አመራርና ፡ በፓትርያርክ ፡ ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ጥረት ፡ በአውሮፓ ፡ አህጉር ፡ የመጀመሪያዋ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋህዶ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ በመሆን ፡ ከ 30 ዓመታት ፡ በላይ ፡ አስቆጥራለች ። የቤተክርስቲያኒቱ ፡ መሥራች ፡ በሆኑትና ፡ በመጀመሪያው ፡ የአውሮፓ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ድካም ፡ ለመንበረ ፡ ጵጵስና ፡ የደረሰች ፡ እንደመሆኑ ፤ ከቅዱስ ፡ ሲኖዶስ ፡ ጋር ፡ ያላትን ፡ ቀጥተኛ ፡ ግንኙነት ፡ ጠብቃ ፡ ኖራለች ። ወደፊትም ፡ በቅዱስ ፡ ሲኖዶስ ፡ ሥር ፡ የምትመራ ፡ የእናት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አካል ፡ መሆንዋን ፡ በድጋሚ ፡ ታረጋግጣለች ።
2. የለንደን ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ እያንዳንዱ ፡ ካህንና ፡ ምእመን ፡ በፖለቲካ ፡ አመለካከቱ ፥ በጎሣው ፥ በቋንቋውና ፡ በትውልድ ፡ አካባቢው ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግበት ፡ መንፈሳዊና ፡ ማኅበራዊ ፡ አገልግሎትን ፡ በእኩልነት ፡ የሚያገኝባት ፡ ሆና ፡ ቆይታለች ። ለወደፊትም ፡ በመሠረታዊ ፡ የወንጌል ፡ ዓላማዋ ፡ ጸንታ ፡ ከማንኛውም ፡ የፖለቲካ ፡ ድርጅት ፡ ጋር ፡ ወገናዊነትን ፡ ሳትይዝ ፡ የምትኖር ፡ መሆኑን ፡ ታረጋግጣለች ።
3. በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋህዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሥልጣን ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ዛሬም ፡ ሆነ ፡ ወደፊት ፡ ከክርስትና ፡ እምነትና ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ በሥልጣን ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ የፖለቲካ ፡ ፓርቲ ፡ ጋር ፡ በማበር ፡ በደል ፡ የሚፈጽሙትን ፤ የሃይማኖት ፡ መሪዎችን ፤ የቤተክርስቲያንን ፡ የውስጥ ፡ ጠላቶችና ፡ የሃይማኖት ፡ ለዋጮችን ፡ ለይቶ ፡ በማውገዝ ፤ አመክንዮ ዘሐዋርያት በአንድ ፡ ቅዱስ ፡ ሲኖዶስ ፡ ሥር ፡ መመራት ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱሳዊና ፡ አማራጭ ፡ የሌለው ፡ መፍትሔ ፡ መሆኑን ፡ ታምናለች ።
4. የለንደን ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአርአያ ፡ ሥላሴ ፡ የተፈጠረውን ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ነጻነትና ፡ እኩልነት ፡ የሚረግጠውን ፤ መንግሥትም ፡ ሆነ ፡ የፖለቲካ ፡ ድርጅት ፡ በጥብቅ ፡ ታወግዛለች ። "አትግደል.." ፡ የሚለውን ፡ አምላካዊ ፡ ቃል ፡ በግፍ ፡ የሚተላለፉትን ፡ በግልጽ ፡ ትቃወማለች ።
5. በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሥልጣን ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ የተቀመጡት ፡ አባ ፡ ጳውሎስ ፤ ሕገ ፡ ወንጌልንና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ቀኖና ፡ አፍርሰው ፡ በማስፈረስ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ሳይሆን ፡ በመንግሥት ወታደርና ፡ በሰው ፡ ሠራሽ ፡ የጦር ፡ መሣርያ ፡ ዘወትር ፡ ታጅበው ፡ ከክርስቶስ ፡ በጎች ፡ የተለዩ ፡ በመሆኑ ፡ ፍሬ ፡ አልባ ፡ መሆናቸውን ፡ በተደጋጋሚ ፡ በግብራቸው ፡ መሥክረዋል ።

   በተጨማሪም ፤ በእርሳቸው ፡ ምክንያት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ዓውደ ፡ ምኅረት ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖቻችን ፡ ደም ፡ በከንቱ ፡ በግፍ ፡ የፈሰሰበት ፡ በመሆኑ ፤ የአባቶችን ፡ መስቀል ፡ ለመሣለም ፡ የሚሽቀዳደሙትን ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ መጠጊያ ፡ አንባ ፡ አድርገው ፡ የኖሩትን ፡ ምእመናን ፡ በማሰናከላቸውና ፡ በማስኮብለላቸው ፤ "ከበጎችህ ፡ የተለየህ ፡ ብትሆን ፡ ጠላታቸው ፡ ነህ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ጠላቱ ፡ ነህ ፡ " ተብሎ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ መተዳደሪያ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፭ ፤ ፻፴፰ እንደተጻፈው ፡ ሁሉም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋህዶ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ አባቶች ፤ በተለይም ፡ የቅዱስ ፡ ሲኖዶስ ፡ አባላት ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ከፓትርያርክነታቸው ፡ እንዲያነሡአቸውና ፡ ተገቢውን ፡ የንሥሐ ፡ ቀኖና ፡ እንዲሰጧቸው ፡ በአክብሮት ፡ እንጠይቃለን ።
6. የለንደን ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባ ፡ ጳውሎስን "ብፁዕ ፡ ወቅዱስ" ፡ ብላ ፡ የማትጠራቸውና ፡ ለፓትርያርክነታቸው ፡ እውቅና ፡ የማትሰጥ ፡ መሆኑን ፡ ትገልጻለች ።
7. የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋህዶ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ቅርስና ፡ ሀብት ፡ በቅዱስ ፡ ሲኖዶስ ፡ መመሪያ ፡ ሰጭነት ፡ በማዕከላዊና ፡ ግልጽ ፡ አስተዳደር ፡ በሚታመኑ ፡ ባለሙያዎች ፡ እንዲጠበቅ ፤ ከምእመናንም ፡ በስለት ፡ በሙዳየ ፡ ምጽዋትና ፥ በተለያየ ፡ የገቢ ፡ ምንጮች ፡ እየተሰበሰበ ፡ በፐርሰንቴጅ ፡ ፈሰስ ፡ እየተደረገ ፡ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ ገቢ ፡ የሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ከአባ ፡ ጳውሎስና ፡ ከጥቅም ፡ አጋሮቻቸው ፡ ገደብ ፡ የለሽ ፡ ዝርፊያ ፡ እንዲድን ፤ እንዲሁም ፡ ከውጭ ፡ የእርዳታ ፡ ሰጭዎች ፡ የሚደረገው ፡ ልገሣ ፡ በቀጥታ ፡ ለታቀደላቸው ፡ ተጠቃሚዎች ፡ እንዲደርስ ፡ ማድረግ ፡ የቅዱስ ፡ ሲኖዶሱ ፡ ኃላፊነት ፡ በመሆኑ ፡ በፓትርያርኩ ፡ "ልዩ ፡ ትዕዛዝ" የሚንቀሳቀሰው ፡ የንብረትና ፡ የገንዘብ ፡ ወጭ ፡ በአስቸኳይ ፡ እንዲያስቆም ፤ በአክብሮት ፡ እንጠይቃለን ።
8. ጥንታዊና ፡ ሐዋርያዊት ፡ እናት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የሚያደረጁበትንና ፡ አብረው ፡ የሚሠሩበትን ፡ መርሐ ፡ ግብር ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ በአገር ፡ ውስጥና ፡ በውጭ ፡ ላሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋህዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ካህናትና ፡ ምእመናን ፡ ጥሪ ፡ ታደርጋለች ፤ ትተባበራለች ።

"....በውስጥ ፡ ባሉት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እናንተ ፡ አትፈርዱምን ? በውጭ ፡ ባሉት ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድባቸዋል ፡ ክፉውን ፡ ከመካከላችሁ ፡ አውጡት."

ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ( ፩ ቆሮ ፥ ም ፭ ፡ ቁ ፲፪ )

"ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች"

መዝ ፡ ( ፷፯ ÷ ቁ ፴፩ )

**ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የካህናትና ፡ የምእመናን ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ።**

## ለኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋህዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለቅዱስ ፡ ሲኖዶስ ፡ ጽ / ቤት

ለመንበረ ፓትርያርክ ፡ ጽ / ቤት

ለጠቅላይ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ጽ / ቤት

ለመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋህዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሰበካ ፡ አስተዳደር ፡ ጉባኤ ጽ / ቤቶች

ኢትዮጵያ ፡

ኢየሩሳሌም

አውሮፓ ፡

አሜሪካ

አፍሪካ

መካከለኛው ፡ ምሥራቅ

አውስትራሊያ